የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ሲያዘጋጃቸው ከቆየው ፖሊሲዎች መካከል በ4ቱ ላይ ነገ እሁድ ታኅሣሥ 18 ቀን 2013 ዓ.ም በዋና ጽሕፈት ቤቱ መስፍን ወልደማሪያም አዳራሽ ያደርጋል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ ለውይይት የሚቀርቡት 4 ፖሊሲዎች የጤና (የብሔራዊ የጤና መድህን ስርዓትን ያካተተ)፣ የአካል ጉዳተኞች ፖሊሲ፣ የሥርዓተ-ፆታ ፖሊሲ እና የሠራተኞችና የሙያ ማኅበራት ፖሊሲ ናቸው፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮችና የተለያዩ ባለድርሻዎች ይገኛሉ፡፡

ኢዜማ ህዳር 26 ቀን 2013 ዓ.ም እና ህዳር 27 ቀን 2013 ዓ.ም በጌት ፋም ሆቴል 8 ፖሊሲዎችን (የማክሮ ኢኮኖሚ፣ የኢንቬስትመንት ፣ የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የገንዘብ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ፣ የአካባቢ ጥበቃና ተፈጥሮ ኃብት ልማትና የማኅበራዊ ከለላ) ፖሊሲዎችን ለውይይት ማቅረቡ ይታወሳል። በተመሳሳይ ባሳለፍነው ሳምንት የትምህርት፣ የውጭ ግንኙነትና ዓለም አቀፍ ትብብር፣ የወጣቶችና የባህል ፖሊሲ ላይ ውይይት ማድረጉ ይታወሳል፡፡

ፓርቲው የኢትዮጵያን ሕዝብ መሰረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳሉ ያላቸውን ከ40 በላይ ፖሊሲዎች በባለሙያዎች ሲያዘጋጅ ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ ሲሆን እስካሁን 12 ፖሊሲዎችን ለባለድርሻዎች ውይይት አቅርቧል። በቀሪዎቹ ፖሊሲዎች ላይም የተለያዩ የኅብረተሰብ ወኪሎችንና ባለድርሻዎችን ማወያየቱ ይቀጥላል።

ፖሊሲዎቹ በውይይቱ የሚገኙትን አስተያየቶች ካካተቱ በኋላ እና በፓርቲው ኮንፈረንስ የኢዜማ ፖሊሲ ተብለው ከፀደቁ በኋላ ለሕዝብ ይፋ የሚደረጉ ይሆናል።